# መሬት አትቆጪ !!

አሥራደው (ከፈረንሳይ)

« መሬት አትቆጪ ቀስ ብዬ እረግጣለሁ » ፤
« ነገ ካንቺ በታች መሆኔን አውቃለሁ » ፤
አቀብ ቁልቁል ስሮጥ ኑሮን ለማሳካት ፤
ድንገት ከተጫንኩሽ አይምሰልሽ ክፋት ፤
ዛሬን ፍቀጅልኝ ያሰብኩበት ልድረስ ፤
የሕይወት ግዳጄን ጉዞዬን ልጨርስ ።

በጀርባሽ ታዝዬ ፤
የኖርኩት ኑሮዬ ፤
ባንቺ ዓይን ሲተመን ፤
ባንቺ ልብ ሲመዘን ፤
ወርድና ርዝመቱ ፤
ስፋት ወይ ጥልቀቱ ፤
ጥቅምና ጉዳቱ ፤
ድፍርስ አተላነት ወይንም ጥራቱ ፤
ድቅድቅ ጨለማነት ወይ ጮርቶ መንጋቱ ፤
እስቲ ምን ይመስላል አጫውችኝ ላንዳፍታ ፤
ላልጨረስኩት ጅምር ለቀሪው ጉዞዬ መላን እንድመታ ።

EthioLion.Com

ያን ዕለት ስመጣ ቤትሽ በእንግድነት ፤
አጫውትሻለሁ ስላለፍኩት ሕይወት ፤
ሕመም በሽታዬን ፤
ቅሬታ ቁጭቴን ፤
ጥማት እርካታዬን ፤
ሃዘን ደስታዬን ፤
ጫወታና ቀልዴን ፤
ቅዠትና ሕልሜን ፤
አልሳካ ብሎ የቀረ ምኞቴን ፤
በጅምር የቀረ ያንጠለጠልኩትን ፤
ያምላክ ፈቃድ ሆኖ ያከናወንኩትን
አንዱንም ሳላስቀር ትንሹን ትልቁን ፤
በጀርባሽ ላይ ሆኜ ያውጠነጠንኩትን ።

አጫውትሻለሁ ያለፈው ዕድሜዬን ሁሉንም ዘርዝሬ ፤
ጉዞዬን ጨርሼ ከንዶቹን ስንተራስ ሲታከተው እግሬ ፤
እስከዛው ታገሺኝ ቀስ ብዬ እረግጣለሁ ፤
ነገ ካንቺ በታች መሆኔን አውቃለሁ ።

ግንቦት ሰድስት ቀን ሁለት ሺህ አንድ ዓ.ም (May 14 2009)
በግንቦት 1997 ዓ.ም. (እ.ኢ.አ.) በግፍ ለወደቁ ወገኖቼ መታሰቢያ ትሁንልኝ ።

EthioLion.Com